# BBC LEARNING ENGLISH
# Essential English Conversation
# Routine:
# What time do you start work?

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንከወን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዚህ ክፍል ስንት ሰዓት ላይ ስራ እንደሚጀመር 'start work' እና ስንት ሰዓት ላይ ስራ እንደሚጨረስ 'finish work' መናገርን ይማርሉ።
ሁለት ሰዎች ስንት ሰዓት ላይ ስራ እንደሚጀምሩ ሲያወሩ ያዳምጡ።

***Judy***
*Hi Paul, when do you start work?*

***Paul***
*I start work at seven-thirty.*

***Judy***
*What time do you finish work?*

***Paul***
*I finish work at five-thirty.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
በመጀመሪያ ጁዲ ፖልን ስንት ሰዓት ላይ ስራ እንደሚጀምር 'starts work' ጠየቀችው። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*When do you start work?*

**ዘሩባቤል**
ፖል ስራ የሚጀምረው 'seven-thirty' አንድ ተኩል ላይ መሆኑን ተናገረ። 'Thirty' ተኩልን የምንጠቀመው ከሰዓቱ በኋላ ምን ያህል ደቂቃ እንዳለ ለመጠቆም ነው። ከአንድ ሰዓት በኋላ ሰላሳ ደቂቃ አልፎ ማለት ነው። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I start work at seven-thirty.*

**ዘሩባቤል**
ከዚያም ጁዲ ፖልን ስንት ሰዓት ላይ ስራ እንደሚጨርስ 'finishes work' ጠየቀችው። ስለጊዜዎች ለመጠየቅ 'when' ወይንም 'what time' መጠቀም እንችላለን። ምንም ዓይነት ልዩነት የላቸውም። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*What time do you finish work?*

**ዘሩባቤል**
ፖል ስራ የሚጨርሰው 'five thirty' አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ እንደሆነ ተናግሯል። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I finish work at five-thirty.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ የተለያዩ ሰዎች ስንት ሰዓት ላይ ስራ እንደሚጀመሩ እና እንደሚጨርሱ ሲነጋገሩ ያዳምጡና እርስዎ ያሉትን ይፈትሹ።
ራየን ስራ የሚጀምረው ሶስት ተኩል ላይ ሲሆን የሚጨርሰው ደግሞ አስር ተኩል ላይ ነው።

*Hi Ryan, what time do you start work?*

*I start work at nine thirty.*

*Ok. What time do you finish work?*

*I finish work at four thirty.*

**ዘሩባቤል**
ሊዝ ስራ የምትጀምረው ሶስት ተኩል ላይ ሲሆን የምትጨርሰው ደግሞ አንድ ተኩል ላይ ነው።

*Hi Liz, when do you start work?*

*I start work at nine thirty.*

*OK. When do you finish work?*

*I finish at seven thirty.*

**ዘሩባቤል**
እሺ፥ አሁን ደግመን እንሞክር። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮቹን ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ይሰማሉ።

*When do you start work?*
*When do you start work?*

*I start work at seven thirty.*
*I start work at seven thirty.*

*What time do you finish work?*
*What time do you finish work?*

*I finish work at five-thirty.*
*I finish work at five-thirty.*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንደሚያስታውሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡ እና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

ስንት ሰአት ላይ ነው ስራ የምትጀምረው?
*When do you start work?*

ስራ የምጀምረው አንድ ተኩል ላይ ነው።
*I start work at seven thirty.*

ስራ የምትጨርሰው ስንት ሰዓት ላይ ነው?
*What time do you finish work?*

ስራ የምጨርሰው አስራ አንድ ተኩል ላይ ነው።
*I finish work at five-thirty.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ግሩም፥ አንድ ሰው ስራ የሚጀመረው እና የሚጨርሰው ስንት ሰዓት ላይ እንደሆነ መጠየቅን እና መናገርን አውቀዋል። ለጁዲ ምላሽ በመስጠት እና እነዚህን ነገሮች የምታከናውነው ስንት ሰዓት ላይ እንደሆነ በመጠየቅ ልምምድ ያድርጉ።

*When do you start work?*
*What time do you finish work?*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ጠቅላላውን ንግግር ያዳምጡና መልስዎን ይፈትሹ።

***Judy***
*Hi Paul, when do you start work?*

***Paul***
*I start work at seven-thirty.*

***Judy***
*What time do you finish work?*

***Paul***
*I finish work at five-thirty.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን በእንግሊዝኛ ስራ ስንት ሰዓት ላይ እንደሚጀመር እና እንደሚጨርስ መጠየቅም መናገርም ይችላሉ። የተማሩትን መለማመድ ያስታውሱ። ጓደኛ ይፈልጉና ስራ ስንት ሰዓት ላይ እንደሚጀምሩ እንዲሁም እንደሚጨርሱ በእንግሊዝኛ መጠየቅን እና መናገርን ይለማመዱ። ለተጨማሪ Essential English Conversation ዝግጅቶች በቀጣይ ክፍላችችን ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018